የመፅሐፉ ርዕስ ፡ ፍፁም ነው እምነቴ
ቀይ ሽብር
የከፍተኛ 15 እውነተኛ ታሪክ
ፀሐፊ ፡ ነሲቡ ስብሐት (አሉላ)
አስተያየት ፡ አጥላው ዓለሙ ከአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ

የመፅሐፉ ጭብጥ በቅድመ ቀይ ሽብር፣ በቀይ ሽብርና በድህረ ቀይ ሽብር ተከፋፍሎ ቀርቧል። በቅድመ ቀይ ሽብር ዘመን ትረካው የልጅነት ሕይወት ትውስታውን የ1966 ዓ.ም. አብዮት ፍንዳታን፣ የንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት በወታደራዊ መንግሥት ሲተካ የነበረውን ሁኔታ፣ የእድገት በሕብረት ዘመቻን፣ ድብቅ የጥናት ክበባት መጀመርና የኢሕአፓን መታወጅ፣ የከተማና የገጠር ቀበሌዎች መመሥረትና ሚናቸው፣ የኢማሌድህ ምሥረታና የሕጋዊ መድረክ መጥበብ፣ ስለ አደፍርስና የዴሞክራሲያ ዕትሞች፣ የ1969 ዓ.ም. እመቃና የኢሕአፓ የውስጥ ክፍፍል ወሬዎች፣ የነፃ እርምጃና የአሰሳ አጀማመርን በቅደም ተከተል ይተርካል።

በቀይ ሽብር ወቅት ትረካው በተለይ በከፍተኛ 15 ስለነበረው የእሥር፣ የግርፋት፣ የስቃይና ግድያ አፈፃፀም በራሱ ላይ የደረሰውን፣ በዐይን ያየውን፣ የገፈቱ ተካፋዮችና በሕይወት ተርፈው ምሥክርነት የሰጡትን ቃል አጠቃሎ በጊዜው በኢትዮጵያ ምድር የተከሰተውን እውነተኛ ሽብር ገጽታ ይተርካል። ቀይ ሽብር እንደማንኛውም ሂደት አድጐ፣ ጐልምሶና አርጅቶ፣ የገረፈውን ገርፎ፣ የገደለውን ቀብሮ ቀስ በቀስ እየቀነሰ ግድያው ወደ እሥራት፣ እሥራት ወደ መፈታት እየተለወጠ ሲሄድ ያሳያል።

ከቀይ ሽብር በኋላ ስለነበረው ስነልቦናዊ ሁኔታ ፀሐፊው የራሱንና የመሰል ወገኖችን እያነሣ ያወሳናል። ሰውን መግደል እንደ ተራ ተልዕኮ የሚወስደው የመንግስቱ ኃ/ማርያም አመራር ከስምንት ዓመት እሥራት በኋላ ጭዳ ስላደረጋቸው ወጣቶች፣ ስለነሱ ተስፋና ስለቤተሰቦቻቸው ጉጉት እንዲሁም ሰቆቃ በቅርብ ተመልካች ዐይን እየተረከ የሀዘኑ ተካፋይ ያደርገናል። ከዘመናትም በኋላ የቀይ ሽብር ቀንደኛ አራማጅ የነበረው ከፈለኝ ዓለሙ በሰው ልጅ ላይ የፈፀመውን ግፍ ደብቆ በደም የቀላውን ታሪኩን እንደ ቆሻሻ ሸሚዝ በአዲስ ኮት ሸፍኖ የስንቱን ሕይወት አጥፍቶ እሱ ግን በነፃነት ለመኖር አሜሪካ ገብቶ እንደተገኘና እንደተጋለጠ እንዲሁም ስለ ፍርዱ ሂደት ያወሳናል።

የመጽሐፉ አፃፃፍ ፍሰት የታሪካዊ ሁኔታዎች ቅደም ተከተልን መሠረት ያደረገ በመሆኑ ታሪኩ ከገፅ ወደ ገፅ እየተቀባበለ ስለሚሄድ ለአንባቢው በጊዜው የተካሄዱትን ልዩ ልዩ ድርጊቶች ትርጉም እንዲያገኝባቸው ይረዳል። ወደ ቀይ ሽብር ያመሩት ሁኔታዎች ቀስ በቀስ እንዴት እየተሰካኩ እንደመጡ በተለይ በጊዜው ላልነበሩና ሁኔታውን ከውስጥ ሆነው ላላዩት ጥሩ ማስገንዘቢያ ነው። በወጣቱ ሊግ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ወጣቶች ሊግ (ኢ.ሕአወሊ) ውስጥ የነበረው ነሲቡ በዘመኑ የነበረውን የትግል ስሜትና መንፈስ፣ አመለካከትና ስነ ልቦናዊ ሁኔታ እንደወረደ ያስተላልፋል። በተመሳሳይ ሁኔታ ላለፉትም ሰዎች ትረካው ጊዜውን መልሰው እንዲኖሩት፣ የጊዜውን ሽታ እንዲያሸቱ፣ በዓይነ ህሊናቸው ድርጊቶችን እንደገና እንዲያዩት፣ በጊዜው የነበረውን ንዴት፣ ሀዘንና ደስታ በመቀስቀስ

እንደገና በዛሬ ህሊና እንዲያስተውሉት ያደርጋል። አፃፃፉ ቀላል በመሆኑ ያለችግር ሃሳቦችን እየያዙ ወደፊት መሮጥ ይቻላል። ፅንሰ ሀሳቦችም በሚገባ ሁኔታ ተገልፀዋል።

ምንም እንኳ ንባቡ በሀሳብ ወደ ኋላ ወስዶ የሚያሠጥም ቢሆንም የመፅሐፉ መልዕክት ለወደፊቱም ትውልድ ጠቀሜታ አለው። ቀይ ሽብር ትውልድን መጨረስ ብቻ ሳይሆን የሀገር ስሜትንና የለውጥ ፈላጊነት መንፈስንም የገደለ ድርጊት መሆኑን ስለሚያስገነዝብ ዳግም እንዳይደገም ያሳስበናል። ኃላፊነት የጐደለው ቡድን የመንግሥት ስልጣን ሲይዝ ሊከተል የሚችለውን የጥፋት ጥልቀት መገንዘብ ያስችላል። የአምባገነን መንግሥት እመቃ ሲበዛ እንዴት ወደ ሚስጥራዊ አሠራርና አለመተማመን እንደወሰደ ያሳያል። እርስ በርሱ የተናቆረው ለውጥ ፈላጊ ትውልድ በግትርነትና ባለማስተዋል እንዴት ለመንግሥቱ ኃ/ማርያም ቡድን ቦታውን ለቆ እንደጠፋ ያሳያል።፤ የዚያም መጠፋፋትና መጠላለፍ ውጤት ለማን እንደበጀ በግልጽ ማየት ይቻላል።

ነሲቡ ያቀረበው ተነባቢ መፅሐፍ ለትውልድ መማሪያ ጠቃሚ ነው። ቀድመው ስለ ጊዜው የትግል ተሳትፎና ዕልቂት እንደፃፉት ሌሎች የኢሕአፓ ትግል ተሣታፊዎች ነሲቡም በተለይ ስለ ከተማው ትግልና የወጣት ድርጅቱን ድርሻ እንደ መስተዋት አሳይቷል። ለዚህም አስተዋፅዎ በጣም አመሰግነዋለሁ። ሌሎችም ታሪክን በትክክል ለትውልድ ለማስተላለፍ እንዴት መፃፍ እንዳለበትም ጥሩ መነሻ ሠጥቷል። መልካም ምሳሌ በመሆኑ ከሌሎች ብዙ ታሪኮች ተጽፈው እንደምናነብ ተስፋ አደርጋለሁ። መፃፍ የምንችል እንትጋ ቀሪው ጊዜ ብዙ አይደለም ! አመሰግናለሁ።

አጥላው ዓለሙ

አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ

ኢኮኖሚክስ መምህር

ታህሳስ 22 ቀን 2007 ዓ.ም.